# ስለ ለቆ መውጣት
# እና
# የአደጋ ጊዜ መጠለያ አስር በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

**Anchorage የአደጋ ጊዜ አስተዳደር ጽ/ቤት**

**ዋና: (907) 343-1400**

**የአደጋ ጊዜ ሁኔታዎች መስመር: (907) 343-4701** **www.muni.org/oem**

### *1. በ Anchorage ቦታ ለቆ መውጣት እና የአደጋ ጊዜ መጠለያ የሚያስፈልጋቸው ዋና አደጋዎች ምንድን ናቸው?*

• **ከባድ የመሬት መንቀጥቀጥ:** የመሬት መንቀጥቀጥ ለ Anchorage በጣም ከባድ እና በተደጋጋሚ የሚከሰት ስጋት ነው፡፡ የደቡባዊ ማዕከላዊ Alaska አነስተኛ የመሬት መንቀጥቀጥ በመደበኛነት ቢያጋጥመውም የሚደርሰው ከትንሽ እስከ ምንም የሆነ ጉዳት ነው፡፡ ሆኖም በ 1964 እንደታየው አይነት ከባድ የመሬት መንቀጥቀጥ የአካባቢው ነዋሪ በርካታ ክፍል ላይ ተጽዕኖ ሊያመጣ እና ዋና የመሰረተ ልማት እና ህንጻዎች ላይ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል፡፡




https://www.ready.gov/earthquakes




• **የጫካ እሳት**: Anchorage ለጫካ እሳት ተጋላጭ የሆነ ማህበረሰብ እንደሆነ የ US የግብርና ጫካ አገልግሎት መምሪያ ገልጿል፡፡ አደጋውን የሚያመጡ መንስኤዎች በከፍተኛ የእሳት አደጋ ሁኔታዎች ወዲያው የሚነድ የተቀላቀለ ጠንካራ እንጨት እና የ ጫካን ያካትታል፡፡ በተመሳሳይ በጫካው አካባቢ ዙሪያ ለወቅታዊ የጫካ እሳት ተጋላጭ የሆኑ የመኖሪያ እና የገጠር ሰፈሮች አሉ፡፡

https://www.ready.gov/wildfires



• **ከባድ:** በደቡባዊ ማዕከላዊ Alaska ከባድ የአየር ንብረት አደጋ ሊያስከትል ይችላል፤ ለምሳሌ ከመብረቅ ጋር የተቀላቀለ ከባድ ዝናብ፣ ከፍተኛ ወይም የሄሪኬን ሀይል ያለው ንፋስ፣ ትላልቅ በረዶ እና ጎርፍ ወይም ከመብረቅ ጋር የተቀላቀለ ጎርፍ፡፡ በተጨማሪ ከባድ የዊንተር አየር ንብረት ከባድ በረዶ፣ በረዷማ ዝናብ እና በጣም ቀዝቃዛ አየር አለው፡፡

• **የሀይል አመንጪ መጠቃቀሚያዎች መቋረጥ:** የተፈጥሮ ጋዝ እና የሀይል ሰጪዎች ጊዜያዊ መቋረጥለተፈናቀሉ ነዋሪዎች የአደጋ ጊዜ መጠለያዎች እንዲቋቋሙ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፡፡ እንደዚህ አይነት ሁኔታዎች በባህሪያቸው ውስን ናቸው ግን ሊስፋፉ ይችላሉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| **የ Chugach ኤሌክትሪክ** | 907-762-7888 | http://www.chugachelectric.com/ |
| **ML&P - የከተማ አስተዳደር ሀይል እና መብራት** | 907-279-7671 | https://www.mlandp.com/ |
| **MEA - የ Matanuska የኤሌክትሪክ ማህበር፡፡** | 907-696-7697 | http://www.mea.coop/ |
| **ENSTAR** | 907-334-7788 | https://www.enstarnaturalgas.com/ |

### *2. በአካባቢዬ ያሉ አደገኛ ሁኔታዎችን እንዴት አውቃለሁ?*

• የሚኖሩበት አካባቢን ሊያጠቃ የሚችል ስጋትን በተመለከተ የአካባቢ መገናኛ ብዙሀን ስርጭት መረጃ ይከታተሉ፡፡

• አማካሪዎች እና ማስጠንቀቂያዎች በኢሜል፣ በሜሴጅ እና ሌላ የመገናኛ ብዙሀን ከህዝብ የደህንነት ኤጀንሲዎች ለማግኘት ነጻ የ NIXLE አገልግሎት ላይ ይመዝገቡ፡፡ የ Anchorage ዚፕ ኮድዎትን ወደ 888-777 በመላክ በቀላሉ ለ NIXLE መመዝበ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ኢሜል እና ሜሴጅ እንዲደርስዎት ለመመዝገብ ወደ NIXLE.com መግባት ይችላሉ፡፡

• በአደጋ ወቅት ወይም አስጊ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ስለሁኔታዎች መረጃ እና ማንኛውም የተለየ መመሪያ ለማግኘት የአካባቢ መገናኛ ብዙሀን ስርጭት እና NIXLE መቆጣጠር ይቀጥሉ፡፡

• በ 2-1-1 መደወል ይችላሉ፤ የስልክ ጥሪ መቆጣጠሪያው ስለሁኔታው፣ ለቆ ስለመውጣት መመሪያዎች እና የአደጋ ጊዜ መጠለያዎች መረጃ ይኖረዋል፡፡

• የ Anchorage የአደጋ ጊዜ ሁኔታዎች መስመር 907-343-4701 በተጎዱ ቦታዎት ለሚኖሩ ሰዎች ቀደም ብሎ የተቀረጸ የዘመነ መረጃ እና መመሪያ መልዕክት ይሰጣል፡፡

• የአደጋ ጊዜ አስተዳደር ጽ/ቤት ድህረ-ገጽ www.muni.org/oem ለወቅታዊ መረጃ እና መመሪያ ጥሩ ምንጭ ነው፡፡



### *3. ለቅቄ መውጣት ካለብኝ እንዴት አውቃለሁ?*

• የህዝብ ደህንነት ሰራተኞች ለቆ መውጣት ከማስፈለጉ በፊት ቀደም ብለው ማስጠንቀቂያ ለመስጠት ይሞክራሉ፡፡ ቅርብ የሆነ አደጋ ሲኖር (የጫካ እሳት ወይም ሌላ አደጋ) ፖሊሶች እና ሌሎች የህዝብ ደህንነት ሰራተኞች በተጎዳው ቦታ የሚኖሩ ሰዎችን ያሳውቃሉ፡፡ ይህን የሚያደርጉት በየሰዉ ቤት በመሄድ፣ ፈቃድ ባላቸው መረጃ አቅራቢዎች ለህዝብ በማሳወቅ ወይም በሁለቱም ሊሆን ይችላል፡፡

• የአካባቢ የዜና ስርጭት እና NIXLE መከታተል – ለቆ የመውጣት ማስታወቂየዎችን እና ማስጠንቀቂያዎችን ይሰጣሉ፡፡

### *4. ለቆ መውጫ መንገዱ የትኛው እንደሆነ እንዴት አውቃለሁ?*




• ለቆ መውጫ መንገዶች በወቅቱ ባሉት እና ወደፊት ይሆናል ተብሎ በሚገመቱ ሁኔታዎች መሰረት እንዲሁም በስጋቱ ወይም በአደጋው ባህሪይ/ይዘት መሰረት በህዝብ ደህንነት ሰራተኞች ይወሰናል፡፡ ለቆ መውጣት ከመታወጁ በፊት ይሆናሉ ተብለው የሚታሰቡ ለቆ መውጫ መንገዶችን ወዲያው ለነዋሪዎች ለመስጠት ሁሉም ጥረት ይደረጋል፡፡

• የእርስዎን ደህንነት ለማረጋገጥ ሲባል የሁኔታዎች መቀያየር ለቆ መውጫ መንገዶች እንዲቀያየሩ ሊያደርግ እንደሚችል ያስታውሱ፡፡ ነዋሪዎች በተገለጹት መንገዶች መጠቀማቸውን ለማረጋገጥ የትራፊክ መቆጣጠሪያ ቦታዎች በ Anchorage ፖሊሶች ይዘጋጃሉ፡፡ እባክዎ ደህንነትዎን ለማረጋገጥ የህዝብ ደህንነት ሰራተኞች የገለጹትን አቅጣጫ ይከተሉ፡፡

### *5. መጓጓዣ ከሌለኝ ወይም ለቆ ለመውጣት እርዳታ ካስፈለገኝስ?*

• አስፈላጊ ከሆነ ለቆ መውጣት ሲታወጅ በከተማው አስተዳደር ባለቤትነት የተያዙ እና ግልጋሎት ላይ የሚውሉ የመጓጓዣ ምንጮች የመጓጓዣ አገልግሎት ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡

• ለቆ ለመውጣት የግል መጓጓዣ ከሌለዎት የህዝብ ደህንነት ሰራተኞች መጀመሪያ ሲያነጋግርዎት መጓጓዣ እንደሌለዎት ማሳወቅ አስፈላጊ ነው፡፡

• መደበኛ የመጓጓዣ አገልግሎት መጠቀም ለማይችሉም ሰዎች ሌላ አገልግሎት (ፓራ-ትራንሲት) ተዘጋጅቷል፡፡



### *6. የቤት እንስሳቱስ?*

• ነዋሪዎች ከቤተሰባቸው ጋር አብረው ስለ የቤት እንስሳቸው ወይም ግልጋሎት ስለሚሰጥ እስሳቸው ለቆ መውጣት ማቀድ አለባቸው፡፡ የቤት እንስሳት ትንንሽ እንስሳት ናቸው ተብሎ ይታሰባል ለምሳሌ ውሻ፣ ድመት ወይም ተመሳሳይ በነዋሪዎች መካከል የተለመዱ እንስሳት፡፡

• የቤት እንስሳት ያልተለመዱ ወይም አደገኛ እንስሳትን አያካትትም ለምሳሌ እባብ፣ ጦጣ፣ የቀንድ ወይም የግብርና እንስሳት እንዲሁም የተላመዱ የዱር እንስሳት አይካተቱም፡፡

• ለቆ መውጣት ሲታወጅ የራሳቸው መጓጓዣ ለሌላቸው ነዋሪዎች የቤት እንስሳቸው ከባለቤቶቹ ጋር በከተማው አስተዳደር በተዘጋጀው መጓጓዣ ይወሰዳሉ፡፡ የቤት እንስሳት ለቆ በመውጣት ወቅት የከተማ አስተዳደር መጓጓዣ በሚጠቀሙበት ጊዜ በማንኛውም ሰአት በባለቤትየው መልካም ቁጥጥር ስር መቆየት አለበት፡፡

• ለቆ ለመውጣት የቤት እንስሳት አቅራቢዎች ማምጣት ስላለባቸው ነገሮች ተጨማሪ መረጃ የ Anchorage የአደጋ ጊዜ አስተዳደር ጽ/ቤት ጋር ይገኛል፡፡

### *7. ፈረሴ እና ሌላ የቀንድ ከብቶቼስ?*



• የከተማ አስዳደር በአደጋ ጊዜ የቀንድ ከብት ወይም የግብርና እስሳትን ለቆ የሚያስወጣበት እና የሚንከባከብበት ምንጭ እና አቅም የለውም፡፡ በአደጋ ወቅት የእንስሳቱ ደህንነት እና ጥበቃ የእንስሳቱ ባለቤት ሀላፊነት ነው፡፡

• የአካባቢው የቀንድ ከብት ባለቤቶች በአደጋ እና በችግር ጊዜ እርስ በእርስ እንዲረዳዱ ተመሳሳይ የድጋፍ ጥምረት እንዲቀላቀሉ ወይም እንዲያደራጁ ይበረታታሉ፡፡

• ስጋት ያስከተሉ ሁኔታዎች በተግባር ከመከሰታቸው በፊት የቀንድ ከብት ባለቤቶች አስቀድመው እንስሳቶቻቸውን እንዲያስወጡ ይበረታታል፡፡



### *8. የአደጋ ጊዜ መጠለያው የሚገኘው የት ነው?*

● የአደጋ ጊዜ መጠለያ ቦታውን የህዝብ ደህንነት ሰራተኞች በተቻለ መጠን አስቀድመው ለነዋሪዎች ይናገራሉ፡፡ የአደጋ ጊዜ አመቻቾች ት/ቤት፣ የከተማ አስተዳደር ቦታ ወይም የግል ቦታ ወይም የኪራይ ቦታ ሊሆን ይችላል፡፡

● እንደ ለቆ መውጫ መንገዶች የአደጋ ጊዜ መጠለያዎች የሚመረጡት በሁኔታው እና በቦታው ቅርበት መሰረት ነው፡፡ ለአደጋ ጊዜ መጠለያነት የሚያገለግለው ቦታ መገኛ እና አይነትን ለመወሰን የሚፈናቀለው ሰው ቁጥርም ከግንዛቤ ይገባል፡፡

● ነዋሪዎችን ማውጣት መጀመሪያ ላይ ወደ ጊዜያዊ የመቀበያ ማዕከል ሊመራ ይችላል በመቀጠል የአደጋ ጊዜ መጠለያ ይዘጋጃል፡፡

● በአጠቃላይ በከተማ አስተዳደር የሚዘጋጁ የአደጋ ጊዜ መጠለያዎች በቀይ መስቀል ይተዳደራሉ፡፡ የተፈናቀሉ ነዋሪዎች በአደጋ ጊዜው መጠለያ የሚያገኙት የምግብ አገልግሎት በመጠለያ አስተዳደሩ ሰራተኞች ይሰራል፡፡

● ወደመጠለያ ምን ማምጣት እንደሚያስልግ ተጨማሪ መረጃ ከቀይ መስቀል ወይም የአደጋ ጊዜ አስተዳደር ጽ/ቤት ይገኛል፡፡

### *9. በአደጋ ጊዜ መጠለያው የቤት እንስሳዬ ከኔ ጋር መሆን ይችላል?*

● የቤት እንስሳት በአደጋ ጊዜ መጠለያ ውስጥ አይገቡም፡፡ የእንስሳት ባለቤቶች በመጠለያው በሚቆዩበት ወቅት የቤት እንስሳቸው ወደእንስሳት ማቆያ እንዲገባላቸው ወይም ጓደኛ እንዲንከባከብላቸው ማድረግ አለባቸው፡፡

● የአካል ጉዳተኛ አሜሪካኖች ህግ በተገደበው እና በተተረጓመው መሰረት በአደጋ መጠለያ እንዲገቡ የሚፈቀድላቸው እንስሳት አገልግሎት የሚሰጡ ውሾች እና አገልግሎት የሚሰጡ ትናንሽ ፈረሶች ብቻ ናቸው (ADA)፡፡https://www.ada.gov/service_animals_2010.htm

● በርካታ ቁጥር ያላቸው ሰዎች እና የቤት እንስሳት የተፈናቀሉበት ለቆ መውጣት ሲኖር የከተማ አስተዳደሩ የአደጋ ጊዜ የቤት እንስሳት መጠለያ ያዘጋጃል፡፡

● የአደጋ ጊዜ የቤት እንስሳት መጠለያ እንደ የቤት እንስሳ ማሳደጊያ አይደለም፤ የእንስሳው ባለቤቶች በአደጋ ጊዜ የቤት እንስሳት መጠለያ ቦታው ለእንስሳቶቻቸው እንክብካቤ እንዲሰጡ ይጠበቃሉ፡፡

● የቤት እንስሳ ባለቤት ማድረግ ስላለበት ነገር ተጨማሪ መረጃ የከተማ አስተዳደር የእንስሳት እንክብካቤ እና ቁጥጥር ማዕከል ጋር ይገኛል ፡፡

### *10. ወደቤቴ መመለስ ያለብኝ መቼ እንደሆነ እንዴት አውቃለሁ?*

● የህዝብ ደህንነት ሰራተኞች ወደቤት መቼ መመለስ እንደሚቻል በዋናነት በመገናኛ ብዙሀን ስርጭት፣ NIXLE እና የማህበራዊ ድህረ-ገጽ በኩል ለነዋሪዎች ይናገራሉ፡፡

● የአደጋ ጊዜ መጠለያ ቦታዎች ነዋሪዎች መቼ ወደቤት ሊመለሱ እንደሚችሉ የሚያስረዳ መረጃ ይለጥፋሉ፡፡

● የመምሪያ ድህረ-ገጾች ለምሳሌ ፖሊስ፣ እሳት እና የአደጋ ጊዜ አስተዳደር ጽ/ቤት መቼ ወደቤት እንደሚመለሱ ለዜጎች ያሳውቃሉ፡፡

**የ Anchorage ፖሊስ መምሪያ**

Facebook https://www.facebook.com/APDInfo
Twitter https://twitter.com/APDInfo
የከተማ አስተዳደር ድህረ-ገጽ http://www.muni.org/departments/police/pages/default.aspx

**የ Anchorage የእሳት መምሪያ**

Facebook https://www.facebook.com/pages/The-Anchorage-Fire-Department
Twitter https://twitter.com/afdinfo
የከተማ አስተዳደር ድህረ-ገጽ http://www.muni.org/departments/fire/pages/default.aspx

**አደጋ ጊዜ አስተዳደር ጽ/ቤት**

Facebook https://www.facebook.com/AnchorageOEM
Twitter https://twitter.com/Anchorage_OEM
የከተማ አስተዳደር ድህረ-ገጽ http://www.muni.org/departments/oem/pages/default.aspx

## ነዋሪዎች በሚከተለው ለሁሉም አደጋዎች እና ችግሮች መዘጋጀት አለባቸው:




☐ ***ስንቅ ማዘጋጀት!***

- ለ 7 ቀናት ወይም ከዛ በላይ የሚሆን ለመጠለያ የሚሆን ስንቅ መስራት እና በፍጥነት ከቤት መውጣት ቢያስፈልግ በእግረ-መንገድ የምትያዝ አነስተኛ ስንቅ መስራት!
- ውሀ፣ ምግብ፣ መድሀኒት፣ ልብስ፣ ጥሬ ገንዘብ፣ የሽንት ቤት መጠቃቀሚያ፣ ንጽህና መጠበቂያ፣ የቤት እንስሳት መንከባከቢያ እቃዎች እና ለተለዩ ፍላጎቶች የሚውሉ (ኢጋዥ መሳሪያዎች የተለዩ ምግቦች ወዘተ)፡፡

☐ ***እቅድ ማውጣት!***

- የሚነጋገሩት እንዴት ነው? የሚወስዱት እርምጃ ምንድን ነው?

☐ ***ማወቅ!***

- ከ Anchorage የህዝብ ደህንነት በሜሴጅ፣ ኢሜል፣ Facebook ወይም Twitter ማስጠንቀቂያ እና ምክር ለማግኘት ለ Nixle ይመዝገቡ፡፡ የእርስዎን MOA ዚፐ ኮድ ለ 888777 ይላኩ ወይም ኦንላይን በ Nixle.com ይመዝገቡ
- የአካባቢ ዜና ያዳምጡ፣ ይመልከቱ እና ይከታተሉ፡፡

እቅድ ማውጣት፣ እግረ-መንገድ የሚያዝ ስንቅ ማዘጋጀት፣ እና መስማትን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ የአደጋ ጊዜ አስተዳደር ጽ/ቤት ጋር ይገኛል፡፡

**የጫካ እሳት ዝግጁነት...**

## ተዘጋጅ፣ በቦታ፣ ሂድ!

☐ ***ተዘጋጅ! እሳት የለመደ እና ዝግጁ ሁን!***

እሳት ቢነሳ ቤትዎ ዝግጁ እንዲሆን የጫካ እሳት ስጋት ከመፈጠሩ በፊት የግል ሀላፊነት ይውሰዱ እና ይዘጋጁ፡፡ ከቤትዎ እንጨቶችን በማስወገድ ሊከላከሉበት የሚችሉት ቦታ ያዘጋጁ፡፡ እሳት የሚቋቋም አጥር መስሪያ በመጠቀም እሳት በሚቋቋም የግንባታ ስራዎች ቤትዎን ያጠንክሩ፡፡ የአደጋ ጊዜ እቃዎችን ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ያሰባስቡ፡፡ ማምለጫ መንገዶችን ያቅዱ እንዲሁም ቤት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ እቅዱን እንደሚያውቁት ያረጋግጡ፡፡




☐ ***በቦታ! ለሁኔታ ተገቢ የሆነ ግንዛቤ ያዳብሩ እና ያሳድጉ!***

የአደጋ ጊዜ እቃዎትን ይጫኑ፡፡ ስለእሳቱ ያለውን አዲስ ዜና እና መረጃ ከአካባቢ ዜና፣ አካባቢ የእሳት መምሪያ እና የህዝብ ደህንነት ጋር ይከታተሉ፡፡

☐ **ሂድ! ቀደም ብለው እርምጃ ይውሰዱ!**

የግልዎን የጫካ እሳት እቅድ ይከተሉ፡፡ ይህ ማድረግ ደህንነትዎን ከመደገፉ ባሻገር የእሳት አደጋዎች እሳቱን ለማጥፋት ምንጮችን በደንብ ለመጠቀም ያስችላቸዋል፡፡

http://www.wildlandfirersg.org/Resident